በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የዓለም ፍጻሜ

## *ክፍል አንድ*


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡00 – 2፡00 ምሽት

**ግንቦት ፲፬ ፳፻፫ ዓ.ም.**

# ዳግም ምጽአቱን መጠባበቅ

- የዓለም ፍጻሜ ትምህርትን ዳግም ምጽአቱን መጠባበቅ፣ የዳግም ምጽአት ምልክቶች፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ ዳግም ምጽአት፣ የሙታን ትንሣኤ፣ የመጨረሻው ፍርድ፣ ማጠቃለያ በሚሉ ንኡሳን ርእሶች ከፋፍለን እንመለከታለን፡፡

- በምድር የምንኖርበት ዋናው ምክንያቱ ለዘላለማዊ ሕይወት መዘጋጀት ነው፡፡ የተሰጠንንም ውድ ጊዜ አሟጠን በትክክለኛው መጠን መጠቀም ዘላለማዊ ሕይወትን ለመውረስ የምናደርገው ዝግጅት ክርስቲያናዊ ጥበብን የተሞላ መሆኑን ያመለክታል፡፡

- ጌታችን ደቀመዛሙርቱን #ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ፡፡; ማቴ 24፡42 በማለት ደጋግሞ አሳስቧቸዋል፡፡

- በተጨማሪም ስለመጨረሻው ፍርድ ማቴ 25፡31-46፣ ጌታችን ስለስንዴውና ስለእንክርዳዱ ያስተማረው ምሳሌ ማቴ 13፡24-30፣ የጌታቸውን መምጣት ስለሚጠብቁ ባሮች ሉቃ 12፡35-40፣ እግዚአብሔርንም ስለማይፈራው መጋቢ ሉቃ16፡1-13፣ ስለ መክሊት ማቴ 25፡14-30፣ ስለወይን አትክልት ሠራተኞች ማቴ20፡1-16፣ ስለ አሥሩ ደናግል ማቴ 25፡1-13፣ ሌሎቹም ዳግም ምጽአቱን የሚያሳስቡን ናቸው፡፡

# ዳግም ምጽአቱን መጠባበቅ…

- ምንም እንኳ በርካታ ሰዎች ሞትን በመፍራት የተነሳ ስለዚህ ከማሰብ የሚርቁ ቢሆንም ሐዋርያት ግን ክርስቲያኖችን #እናንተ ደግሞ ታገሡ፥ ልባችሁንም አጽኑ፤ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና። ወንድሞች ሆይ፥ እንዳይፈረድባችሁ እርስ በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ እነሆ፥ ፈራጅ በደጅ ፊት ቆሞአል።; ያዕ 5፡8-9። በማለት ስለዚህ ማሰብ የበለጠ ንቃትን የሚፈጥር ጠቃሚ ሕይወት መሆኑን ይመክራሉ።
- የቀደሙት ክርስቲያኖች የጌታችንን ዳግም መምጣት በንቃት ይጠባበቁ ነበር።
- ምጽአቱንም ዙሪያቸውን በከበባቸው የጸና መከራ ውስጥም ሆነው ይጠባበቁት ነበር፤ለአንድ ቀንም ቢሆን ውሎ ስለማደሩ እርግጠኛ ሆኖ የሚያውቅ የለምና።
- ይህንንም ከመጀመሪያው ሰማዕት ከቅዱስ እስጢፋኖስ ጀምሮ፤ የቅዱስ ጳውሎስንና የቅዱስ ጴጥሮስን፤ ቅዱስ ጊዮርጊስን … በኔሮን፤ በድምጥያኖስ፤ በዲዮቅልጥያኖስ… ቄሳሮችና በሌሎችም የመከራ ዘመናት በፍጹም ጽንአት እርሱንም በደስታ ለመገናኘት በመፈለግ የጌታችንን መምጣት በመጠባበቅ አርፈዋል።
- መከራው ጋብ ካለበትና ኢአማኒነትም እየተዳከመ ከመጣበት ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የክርስቲያኖች ሕይወት እየቀዘቀዘ ሄዷል፤ ምጽአቱንም በመዘናጋት መጠባበቅ ታይቷል።

# የዳግም ምጽአት ምልክቶች

- መጽሐፍ ቅዱስ ቀኑንና ሰዓቱን ባይገልጽልንም የጊዜውን መቃረብ የምንረዳባቸው ምልክቶችን ግን ሰጥቶናል፡፡

- ጌታችንም #ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ። እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።; ማቴ 24፡32-34 በማለት ክስተቶችን መመርመር ምን ያህል ወደ ምጽአቱ እንደተቃረብን ምልክት ሊሰጠን እንደሚችል አስተምሮናል፡፡

- ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው እንዲሁም ደቀመዛሙርቱ ባስተማሩን ትምህርት መሠረት የጌታችን ዳግም ምጽአት መቃረብ የሚያመለክቱ የሚከተሉትን ምልክቶች እናገኛለን፡፡

1. *የብርሃን ወንጌል በዓለም ሁሉ መሰበክ*

- ጌታችን ከምጽአቱ አስቀድሞ ዓለም ሁሉ በርሱ ለማመን የሚያስችለው ዕድል እንደሚያገኝ ተናግ[ ል፡፡ #ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።; *ማቴ 24፡14፡፡*

# የዳግም ምጽአት ምልክቶች…

2. *የእምነት ፍጹም መዳከም*

- የጌታችንን ትምህርት ለማወቅ ዕድሉ ቢኖርም ሰዎች ግን እንዳላወቁት ይሆናሉ፤ ስለዚህ ጌታችንም #ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?; *ሉቃ 18፡8፡፡* በማለት ጠይቆናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም እንደተናገረው #ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፡፡ እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ፡፡; *2ኛ ጢሞ 4፡3-4፡፡* ብሎአል፡፡

- ወደ ዓለም ፍጻሜ መቃረቢያ እውነት በሆነው በትምህርተ ሃይማኖት፤ በሞራልና በሥነ ምግባር እጅግ ቸልተኞች ይሆናሉ፡፡

- ሰዎች ያስደስተናል ወይም ያረካናል የሚሉትን ብቻ የሚሰሙ ይሆናሉ፤ ይኸም አመለካከት ወደሚከተለው አደጋ ይመራል፡፡

3. *የሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች መምጣት*

- ጌታችንም #ብዙዎች፡፡ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ፡፡ … ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ፡፡… ብዙዎች፡፡ እኔ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፥ ብዙዎችንም ያስታሉ፡፡; *ማቴ 24፡5፤ ማቴ 24፡24፤ ማር 13፡6፡፡* ብሏል፡፡

# የዳግም ምጽአት ምልክቶች…

- ራእየ ዮሐንስም የክርስቶስ ተቃዋሚው ሐሳዌ መሲሁ (666) ስለ ሚያደርጋቸው ሐሰተኛ ተአምራት ያስረዳል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ተአምራቶቹ እውነተኛ ተአምራት እንዳልሆኑ በክፉ መናፍስት በማስመሰል የሚፈጸሙ እንደሆኑ ገልጦላቸዋል፡፡ <u>*ራእ.ይ 13፡13-15፤ 2ኛ ተሰ 2፡9፡፡*</u>

4. <u>*አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደማመን ይመለሳሉ*</u>

- ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው የብዙዎች ከክርስትና መራቅ የአይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ማመን ከመመለስ ጋር ይከሰታል፡፡ #ወንድሞች ሆይ፥ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ ይህን ምሥጢር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፤ የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤ እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡ መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል፡፡ ኃጢአታቸውንም ስወስድላቸው ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው፡፡ በወንጌልስ በኩል ስለ እናንተ ጠላቶች ናቸው፥ በምርጫ በኩል ግን ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸው፤ እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና፡፡ እናንተም ቀድሞ ለእግዚአብሔር እንዳልታዘዛችሁ፥ አሁን ግን ከአለመታዘዛቸው የተነሣ ምሕረት እንዳገኛችሁ፥ እንዲሁ በተማራችሁበት ምሕረት እነርሱ ደግሞ ምሕረትን ያገኙ ዘንድ እነዚህ ደግሞ አሁን አልታዘዙም፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን በአለመታዘዝ ዘግቶታልና፡፡ የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም፡፡; <u>*ሮሜ 11፡25-33፡፡*</u>

# የዳግም ምጽአት ምልክቶች…

5. *ክፋትና ሕገ ወጥነት ይበራከታል*

- ጌታችን #ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች::; *ማቴ 24:12::* እንደለ:: ቅዱስ ጳውሎስም #ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ:: ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ::; *2ኛ ጢሞ 3:1-5::* ብሎአል::

- እግዚአብሔርን መሻት ይጠፋል፤ ትምህርቱን ቸል ይሉታል ወይም ፈጽመው ይተውታል፤ ክርስቲያናዊ ትውፊትና ባህል ይናቃል፤ የቤተክርስቲያን ስሪቶች፤ ዜማዎችዋ፤ በዓላቶችዋ እንደ ጥንታዊ ታሪክ ብቻ ይቆጠራሉ::

- አጠቃላይ ገጽታው *በዘፍጥ 6:5-11* የተጻፈውን ይመስላል:: #እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ:: እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ:: … ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች ምድርም ግፍን ተሞላች::; ተመሳሳይ ሁኔታም ከዓለም ፍጻሜ በፊት ይፈጠራል::

# የዳግም ምጽአት ምልክቶች…

6. *ምትሐትና ጥንቆላ… የባዕዳን አማልክት አምላኪዎች ድርጊት ይስፋፋል*

- የበርካታዎች አእምሮ የእግዚአብሔር ላልሆነ ነገር ይገዛል፡፡ #መንፈስ ግን በግልጥ፡፡ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው…; *1ኛ ጢሞ 4፡1፡፡* እንደሉ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም በራእይ 9፡2-21፤ 16፡13፤ 18፡23ክፉ መናፍስት በሰው ሕይወት ውስጥ ስለሚሠሩት ነውር ተናግ[ል፡፡ እነዚህንም #ስለ እጃቸው ሥራ ንስሐ አልገቡም፤ ስለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ስለ አስማታቸው ወይም ስለ ዝሙታቸው ወይም ስለ ስርቆታቸው ንስሐ አልገቡም፡፡; ብሎ ጽፎአል፡፡ *ራእይ 9፡20-21፡፡*

7. *በእግዚአብሔር ያመኑ መከራቸው ይበረታል*

- ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ሥልጣንና ኃይል እንዳይነገር በሚሹና በራሳቸው ችሎታ በሚታመኑ ሁሉ ዘንድ የተጠሉ ይሆናሉ፡፡

- በእግዚአብሔር ማመን ይከስማል፤ ሃይማኖታቸውንም አጽንተው ለመያዝ የሚሹም ከማኅበረሰቡ እየተገለሉ ይሄዳሉ፡፡ የገዛ ቤተ ሰዎችም ሳይቀሩ ጠላት ይሆናሉ፡፡ #በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፡፡; … *ማቴ 24፡ 9-10፤ ማር 13፡12-13፤ ሉቃ 21፡16፡፡*

# የዳግም ምጽአት ምልክቶች…

8. *<u>በማኅበራዊ ሕይወት አጠቃላይ መናጋት ወይም አለመረጋጋት ይፈጠራል</u>*

- ደም አፋሳሽ ጦርነቶችና የተለያዩ አደጋዎች ጫፍ ይደርሳሉ፡፡ ሰዎችም ከመከራው ክብደት የተነሳ ይዝላሉ ይደክማሉ፡፡ በራሳቸው ችሎታ መከራውን መkkም ይሳናቸዋል፡፡ ባለማመናቸውም የተነሳ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው እንኳ ፊታቸውን ወደርሱ አይመልሱም፡፡
- #ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው፡፡; *<u>ማቴ 24፡6</u>*
- ሰዎችም በዚህ ንስሐ ከመግባት ይልቅ ልባቸው እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም ይኸንኑ አስመልክቶ #ለቀደመውም ዓለም ሳይራራ ከሌሎች ሰባት ጋር ጽድቅን የሚሰብከውን ኖኅን አድኖ በኃጢአተኞች ዓለም ላይ የጥፋትን ውኃ ካወረደ፥ … ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን፥በደለኞችንም ይልቁንም በርኵስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል፡፡; *<u>2ኛ ጴጥ 2፡5-9፡፡</u>*
- #ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ፡፡ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ…; *<u>ማቴ 24፤ ማር 13፤ ሉቃ 21፡፡</u>*

# የክርስቶስ ተቃዋሚ - ሐሳዌ መሲሕ... አውሬው

*አውሬው - ሐሳዌ መሲሕ - የክርስቶስ ተቃዋሚ (ዎች)*

- ከባሕር የሚወጣ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ያሉት ነው። *ራእ 13፡1-ፍም*

- አሥሩ ቀንዶች ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱት ሹማምንት ሲሆኑ ሰባቱ ራሶች ደግሞ በዋነኛነት የሚደግፉት አገሮች ፋርስ/ኢራን፣ ባቢሎን/ ኢራቅ፣ ጽርዕ/ግሪክ፣ ሜዶን/ ፣ ግብጽ፣ ሮምና ኢየሩሳሌም እና በስፋትና በአዋጅ የሚፈጸሙ ኃጢአቶች ናቸው።

- ሰባቱም ኃጢአቶች ኃጢአተ አዳም - ፈጣሪ ነኝ ማለት፣ ቅትለተ አቤል - የሰው አእምሮ በጥላቻ ይሞላል፣ የባቢሎን ግንብ - የቴክኖሎጂ መስፋፋት ለአውሬው የሚያደርገው አስተዋጽኦ፣ ግብረ ሰዶም - በመላው ዓለም ይቀጣጠላል፣ ኃጢአተ እስራኤል - የሰይጣን አምልኮ፣ ቅትለተ ዘካርያስ - ሄኖክና ኤልያስ ይገደላሉ፣ ሞተ ወልደ እግዚአብሔር - የንጹሐን ክርስቲያኖች በግፍ መጨፍጨፍ ናቸው። *ዘፍጥ 1፡26፣ 2፡3-17፣ ዕብ 11፡4፣ ኩፋሌ 5፡14፣ 2ኛ ተሰ 2፡5፣ ዘፍጥ 19፡1፣ ዘሌዋ 18፡22፣ ሮሜ 1፡20-27፣ ዘጸአ 20፡6፣ ሉቃ 1፡8-67፣ ዕብ 7፡27፡፡* ይነበቡ።

- መለያ ቁጥሩ 666 ነው።- የዕለተ ዓርብ ፍጥረት ወንድ ሰው ነው። ወንዶች 666 አሥራው አላቸው። ኪሞፒዩተር ወይስ ሰው? ሰው ነው።

- ወደፊት ምልክቱን በእጅና በግንባር ማድረግ ግድ ይሆናል። የሌላቸውም መግዛትም ሆነ መሸጥ ይከለከላሉ።

# የክርስቶስ ተቃዋሚ - ሐሳዌ መሲሕ… አውሬው

- በመጽሐፍ ቅዱስ “የክርስቶስ ተቃዋሚ” የሚለው በአንድ በኩል ከክርስቶስ ትምህርት የተለዩትን ሁሉ የሚመለከት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሐሳዌ መሲሑን ወይም አውሬውን - ሰው የሚመለከት ትርጉም ይዞ እናገኘዋለን፡፡

- የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው መምጣት የክርስቶስ ምጽአት መቅረቡን የሚያረጋግጥልን ወሳኝና የመጨረሻው ምልክት ነው፡፡

- የክርስቶስ ተቃዋሚውን አስመልክቶ ቅዱስ ጳውሎስ #ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥አይደርስምና፡፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው፡፡ ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ፥ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ አይላችሁምን? በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ፡፡ የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ፡፡ በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው፡፡ ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል፡፡; *2ኛ ተሰ 2 ፡ 3 - 11* በማለት ገልጧል፡፡

# የክርስቶስ ተቃዋሚ - ሐሳዌ መሲሕ… አውሬው

- በርካታ ውጫዊ ምንጮችና ምክንያቶች የሚመጣውን የክርስቶስ ተቃዋሚ ኃይል ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

- በአውሬው ዘመን የኒውክሌርና የባዮሎጂካል መሳሪያዎች፤ አስጨናቂና አስፈሪ የሆኑ ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ድቀቶች በሰው ልጅ ላይ ታላቅ ሸክም ይሆናሉ፡፡ መንግሥታትም ወደ ውድቀት ጫፍ ይደርሳሉ፤ በየአገሩም ሁከት፤ አመጽና ብጥብጥ ይስፋፋል፡፡

- በዚህም መካከል ሐሳዌ መሲሑ “የሰው ልጆች መድኃኒት - መፍትሔ” ነኝ ብሎ ይመጣል፡፡ አስጨናቂና አስፈሪ የሆኑ ተቋማትም ዓለም አቀፋዊ ተጽእኖዎችንና የበላይነትን ለመፍጠር በማለም የሐሳዌ መሲሑ አጋር ወይም ረዳት ሆነው ይቆማሉ፡፡

- በሚደረግለትም እገዛ በመጠቀም አውሬው በመገናኛ ብዙኃን በመታገዝ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የለውጥ መርሐ ግብሮችን ያከናውናል፡፡ አውሬው እንደ ሌኒንና ሒትለር የተሳለ አንደበት ያለው ተናጋሪ ስለሆነ ዓላማውና እቅዱም ካከተቱአቸው ቁሳዊ አስተሳሰብ የተነሳ ሙሉ በሙሉ በዓለም ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል፡፡

# የክርስቶስ ተቃዋሚ - ሐሳዌ መሲሕ… አውሬው

- በአንድ በኩል የክርስትና ሃይማኖት ተቃዋሚ የሆኑት አይሁድ አውሬውን ለረጅም ዘመናት ሲጠብቁት የነበሩት መሲህ አድርገው ሲቀበሉት በሌላ በኩል ደግሞ በርካታዎች አውሬው ጦርነትንና በዓለም የሚታየውን ጭንቅና መከራ ሁሉ በማስወገድ አጠቃላይ መረጋጋትንና መደላደልን ያመጣልናል ብለው ያስባሉ።

- በዚህ የተነሳ ሕዝቡ በፊታቸው ያለውን ማየት እስኪሳናቸው ድረስ ይታወራሉ። ቅዱስ ጳውሎስ "ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም፤ የጌታ ቀን፥ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፥ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና። ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም፥ሁላችሁ የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም፤ እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ።" *1ኛ ተሰ 5፡1-6።* በማለት አሳስቧል።

- የክርስቶስ ተቃዋሚው በሚጨብጠው ፓለቲካዊ ሥልጣንና በሚመለከተው ውጫዊ ለውጥ ብቻ የሚረካ አይሆንም። መለኮታዊ ኃይል እንዳለው አድርጎ ራሱን በመቁጠር በሁሉ መመስገንን ይሻል።

# የክርስቶስ ተቃዋሚ - ሐሳዌ መሲሕ... አውሬው

- አውሬው "ጊዜ ያለፈበት፣ ያረጀ ያፈጀና ውጤት አልባ ነው" ብሎ በሚቆጥረው የክርስትና ትምህርት ምትክ አዲስ አስተሳሰብን፣ አዲስ ሃይማኖትን፣ አዲስ ሥነምግባርን ለዓለም ያስተዋውቃል ወይም ያውጃል፡፡

- በዚህ አስተሳሰብም በመኮፈስ ራሱን "እግዚአብሔር" አድርጎ ያቀርባል መለኮታዊ አምልኮ እንዲፈጸምለትም በቤተመቅደስ ይቀመጣል፡፡

- ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው የክርስቶስ ተቃዋሚ በሰይጣን፣ በሚሠራቸው ሐሰተኛ ምልክቶችና ተአምራት፣ እንዲሁም በኋላ በሚጠፉና ቅድስና በጎደላቸው የማታለል እንቅስቃሴዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ ውጤታማ ይሆኑለታል፡፡

- አውሬው በምልክቶቹና በተአምራቱ ብዙዎችን ሊያታልል ስለሚችልበት ዘዴው ብቻ ሳይሆን አውሬው አገዛዙን ስለሚያጠናክርበትም ሳይንሳዊ ግኝቶችና ውጤቶችም በጥልቀት መመርመርና መገንዘብ ይጠበቅብባል፡፡ "የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው፡፡" *ራእይ 13፡15፡፡*

# የክርስቶስ ተቃዋሚ - ሐሳዌ መሲሕ… አውሬው

- አውሬው ከሁሉም በላይ ሁሉን የሚሰልልበትና የሚከታተልበት የተወሳሰበ ዘዴ ያለው ሲሆን በዚህም የእያንዳንዱን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል፡፡

- መግዛትና መሸጠ የሚፈልጉ ሁሉ መግዛትም ሆነ መሸጥ የሚያስችላቸውን ፈቃድ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ “የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል፡፡ ጥበብ በዚህ አለ፡፡” *ራእይ 13፡17፡፡*

- በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነቱን ለማጉላትና ፓለቲካዊ ኃይሉን ለማጠናከር የሬድዮ፤ የቴሌቪዢንና የኅትመት ውጤቶችም ሰፊ ሽፋን ለክርስቶስ ተቃዋሚ ይሰጣሉ፡፡

- በክርስቶስ ተቃዋሚ ልዩ መሪነት ላይ ጥያቄ የሚያነሳ ወይም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ የማይስማማ ማንኛውም ሰው ይገለላል፤ ይታሰራል እንዲሁም ለኅብረተሰቡም ጎጂ እንደሆነ ተቆጥሮ በመገደልም ቢሆን ይወገዳል፡፡

- አውሬው በድርጊቱ ክርስቲያኖችን ሲያሰቃዩ የነበሩ እንደ ኔሮን፤ ድምጥያኖስ… ያሉ የሮም ቆሳሮች ይመስላል፡፡ አውሬው በክርስቲያኖች ላይ የሚያደርጋቸው ተጽእኖዎች ብቻውን ሳይሆን በሚፈጥራቸው ኃይሎችም በኩል ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

# የክርስቶስ ተቃዋሚ - ሐሳዊ መሲሕ… አውሬው

- የሮም ቄሳሮች በየግል ሕይወታቸው ሐሰተኞች፤ ሥነ ምግባር አልባና ጨካኞች እነደነበሩ ሁሉ ይህም አውሬ እንዲሁ ይሆናል።

- በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው አውሬው በምድር ላይ ለ42 ወራት ወይም ለ3 ዓመት ተኩል ይገዛል። የአውሬውም አገዛዝ በጌታችን ዳግም መምጣት፤ በሙታን መነሳትና፤ በመጨረሻው ፍርድ ይጠናቀቃል። *ዳን 7:25፤ ራእ 11:2-3፤ ራእ 12፤13፤ ራእ 13:5።*

- ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ ለእውነት ምስክር ስለሚሆኑት ስለሁለቱ ምስክሮች (ሄኖክና ኤልያስ፤- *ዘፍጥ 5:23፤ 2ኛ ነገ 2:11*) መምጣትና የእውነት ምስክር መሆን፤ ተአምራትን ማድረግ ሥራቸውንም ሲፈጽሙ በክርስቶስ ተቃዋሚ ስለመገደላቸው ጽፎልናል።

- በእነዚህ ጊዜያት የሚሆኑ ሁኔታዎች ሁሉ ግልጽ ቢሆኑም መመልከት የምንችለው ግን እንደ መንፈሳዊነታችን መጠን ነው። በቁሳዊ ፍላጎቶቻቸው መሟላት ብቻ የተሸፈኑ ሰዎች በዓይናቸው ፊት የሚደረገውንም ሆነ ዓለምም ወዴት እያመራች እንደሆነ መመልከት አይችሉም። ጌታችን በዚሁ የተነሳ ነበር ደቀመዛሙርቱን “ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ እንደ ወጥመድ ይደርስባቸዋልና። እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ።” *ሉቃ 21:34-36።* በማለት ያስጠነቀቃቸው።

እኛን በቸርነቱ ይጠብቀን!!!

ክፍል 2 - ይቆየን።